
## ማመልከቻዎን ማስገባት

አባክዎን ይህን ቅጽ በአካል አሊያም በፖስታ ቤት በኩል አድርገው ከታች ባለው አድራሻ በኩል ይላኩት።.

Metropolitan Police Department
Office of Recruiting Outreach
300 Indiana Avenue, NW
Room 4005
Washington, DC 20011

ከዴት ፕሮፋይል/ታሪክ



## ኮማንደር
## ሮበርት ጄ. ኮንቲ

ስድስተኛ አውራጃ


ኮማንደር ሮበርት ጄ. ኮንቲ III ተወልደው ያደጉት በዋሽንግተን ዲሲ. ውስጥ ነው። ትምህርታቸውን ያከናወኑትም ቻርልስ ያንግ የተባለ ሂለመንታሪ ትምህርት ቤት፤ ብራውኒ ጁኒየር ሀይስኩል፤ እንዲሁም ከስፒንጋረን ሲኒየር ሀይስኩል ደግሞ በከፍተኛ ማህረግ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። በህዳር ወር 1989 አመተ ምህረት ላይ እንደ ከዴት ፖሊስ ሆነው ሜትሮፖሊተን ፖሊስ ክፍል ከገቡ ከሶስት አመት በኋላ ቃል መሃላ የገቡ የፖሊስ ክፍሉ አባል ሆኑ። ወዲያውን ማህረጎቹን በሙሉ በተሎ በመሾም ከአንድ የክብር ማህረግ ወደ ሌላው አለፉ፡ በ1997 ሰርጀንት ሆነው ለመሾም በቁ፣ 2000 ሎቲናት ሆኑ፣ በጥር 2004 ካፒቴን ሆኑ።

ለስራ ያላቸውን ትጋት፣ ጠንካራ ሰራተኝነት፣ ለስራቸው ያደሩ መሆናቸውን ሲገነዘቡ ህውቅና በመስጠት የፖሊስ ዋና ሃላፊ የሆኑ ቺፍ ቻርልስ ሄች. ራምዚ በነሐሴ 2004 ላይ የሁለተኛ የፖሊስ አውራጃ ኮማንደር አድርገው ሲሾሟቸው ይህም በዲፓርትመንቱ ታሪክ ውስጥ በእድሜ ከሁሉ ያነሱ ወጣት ኮማንደር እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። በሚያዝያ 2006 ላይ ኮማንደር ኮንቲ ወደ ተለየ ኦፕሬችን ዲቪዥን ተዘዋወሩ እዛም የታክቲካል ፔትሮል፣የተለዩ ዝግጅቶችን፣ እንዲሁም የትራፊክ ደህንነት ሰራዎችን በበላይነት በመቆጣጠር አላፊነት ሰርተዋል።

በስራ ታሪክ ዘመናቸው ሁሉ፡ ኮማንደር ኮንቲ በርከት ባሉ የተለያዩ የስራ ምድቦች ላይ ተመድበው ሰርተዋል፤ በሶስተኛ አውራጃ እንደ ፒትሮል ሹም ሆነው፣ በሁለተኛው አውራጃ፣ እንዲሁም በስልጠና አካዳሚው ውስጥ እንደ ሰርጀንት ሆነው አገልግለዋል። ከዚህ በተጨማሪም፡ እንደ ሎቲናንት ሆነው፡ በሁለተኛው አውራጃ፣ሪጅናል ኦፕሪሽኖች ኮማንድር-ሂስት፣ እንዲሁም በሂንተለጀንስ ቅርንጫፍ ውስጥ አገልግለዋል። የሁለተኛው አውራጃ ኮማንደር ሆነው ከመሾማቸው በፊት፡ በጭካኔ ወንጀሎች ቅርንጫፍ ውስጥ እንደ ሀላፊ ካፒቴን ሆነው ያገለገሉ ሲሆን ቅርንጫፉም የሚመረምራቸው ጉዳዮች ቤት ውስጥ የሚፈጸፍ የነፍስ ግድያንዎችን፣ የጾታን ድፍረትን፣ እንዲሁም ሌሎች ከተማው ውስጥ ከዳር እስከ ዳር የሚከናወኑትን ከፍተኛ ወንጀሎች በአላፊነት ይከታተሉ ነበር።

ኮማንደር ኮንቲ የማኔጅመንት ኮሌጅ የህግ አስከባሪ አስተዳደር ህኒስቲትዩት እና ከሲኒየር የፖሊስ ማኒጅመንት ህንስቲትዩት (ሲኤምሃይፒ) የፖሊስ ከፍተኛ ምርምር ፎረም፡ ቦስተን ማሳቹሴትስ ውስጥ ተምረው ጨርሰዋል። እሳቸው በእራሳቸው የስራ ፊልድ ትምህርር በመቀጠል የሚያምኑ ኮማንደር ሹም በመሆናቸው፡ በአሁኑ ወቅት የፖሊስ ሳይንስን ጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ እያጠኑ ይገኛሉ። እስከዚህ ቀን ድርስ፡ ኮማንደር ኮንቲ ከዲፓርትመንቱ ውስጥ ሁሉ ከፍተኛ ማህረግ ያላቸው ፖሊስ ከዴት ናቸው፤ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ሳውዝሂስት ዲሲ. ውስጥ ለስድስተኛው አውራጃ በኮማንደርነት እያገለገሉ ይገኛሉ።

ከዴት ፕሮፋይል/ታሪክ



## ሲኒየር የፖሊስ ሹም
## ዋለስ ኤል. ብራድፎርድ

ሜትሮፖልተን ፖሊስ አካዳሚ

ሲኒየር ፖሊስ ሹም (ሲፒኦ) ዋሊ. ብራድፎርድ በመጀመሪያ ደረጃ በአባልነት ወደ ኤምፒዲ እንደ ከዴት ፖሊስ ሆነው የገቡት በሰኔ ወር 1965 አመተ ምህረት ነው። በዛን ወቅት የነበረው የጀማሪ ሰራተኛ ደሞዝ በአመት 3,680 ዶላር ነበር። የፖሊስ ከዴት እንደ መሆናቸው መጠን፡ ሲፒኦ ብራድፎርድ መርማሪ ሂክ ቢሮ፣ ዋረንት ስኳድ ውስጥ፣ አውቶ ስኳድ ውስጥ፣ አስራሁለተኛው ክልል ውስጥ፣ እንዲሁም የዋናው መሪ ቢሮ ውስጥ ሰርተዋል። የፖሊስ አካዳሚ ውስጥ ገብተውም ተምረዋል እንዲሁም እንደ ፖሊስ ራዲዮ ዲስፓቸር ሆነውም ሰርተዋል።

በነሐሴ ወር 1998 ላይ ብራድፎርድ ሹም ወይም ኦፊሰር ሆነው ለመስራት ቃለመህላ ገቡ፤ ከዛም ወደ አስራሁለተኛው ክልል (ማለትም በኋላ ላይ አምስተኛ አውራጃ ተብሎ የተሰየመው ማለት ነው) ተመድበው መስራት ጀመሩ፡ እዛም የመታያ/ፕሮቤሽነሪ ግዜያቸውን እግረኛ ፔትሮል ሹም ሆነው፣ ስኮት መኪና ሪሊፍ ሹም ሆነውና ስቴሽን ፔትሮል ነጠላ ሲስተም ሹም ሆነው ሰርተዋል።

በ1972 ኤስፒኦ ብራድፎርድ ሰርጀንት ለመሆን የሚያበቃቸውን የስራ ህድገት ፈተና ተፈትነው አለፉ፤ ከዚያም በዚያው አመት ውስጥ በነሐሴ ወር የመጀመሪያው ፖሊስ ከዴት ሆነው የሰርጀንት ማህረግ ተሰጧቸው ተሾሙ። በዛው አመት ነሐሴ ወር በሁለተኛው የሰርጀንቶች ክፍል ውስጥ እድገት ተሰጣቸው፤ ከጥቂት ቀናት በኋላም የ25ኛ የልደት አመታቸውን ያዙ ይህም በወቅቱ ኤምፒዲ ውስጥ በስራ እድገት ከፍ ካሉት በእድሜ ከሁሉም አነስተኛ እሳቸው ብቻ ነበሩ።

የሰርጀንትነት ማህረግ ካገኙ በኋላ በአንደኛው አውራጃ እንዲሰሩ ተመደቡ ህዛም ለሚቀጥሉት 19 አመታት ቆይተው ሰርተዋል። በአንደኛው አውራጃ እየሰሩ እንዳሉ ሲፒኦ ብራድፎርድ በእያንዳንዱ ሶስት ሴክተሮች ውስጥ በመስራት ተሳትፈዋል፤ በዲሲ. ውስጥ የመጀመሪያው ውጤታማ የማህበረሰብ እራሱን በራሱ የመቻል ፖሊሲ. ፕሮግራምን በመንደፍና ተግባራዊ በማድረግ ያገለገሉ ሲሆን፤ በዛን ወቅት ይህ ፕሮግራም "ቢት 26" በመባል ነበር የሚታወቀው። ቢት 26 የሚያካትታቸው ከነበሩ አዳዲስ ሀሳቦች ማምጣት መካከል እንደ የማህበረሰብ ኒውስሌተር፣ የስልክ ትሪ፣ እንዲሁም የብሎክ ካፒቴን ፕሮግራሞች ጥቂቶቹ ናቸው።

በ1991 በአድናቂዎቻቸው አማካኝነት ከተደረገላቸው ትልቅ መሸኛ በኋላ፡ ብራድፎርድ በ1994 ወደ ዲፓርትመንቱ ሲኒየር ፖሊስ ሹም በመሆን ተመልሰው፡ አካዳሚው ውስጥ የኤምፒዲ አዳዲስ ቅጥሮችን በተለያዩ ቴክኒኮችና ፕሮግራሞች ላይ ስልጠና በመስጠት መስራት ጀመሩ። በ2001 " ዋሊ. ቦርድን" በመፈልሰፋቸው ምክንያት የአቺቭመንት ሜዳል ተሸልማዋል፤ ይህም መሳሪያ የፖሊስ ሹማምንቶች " ስሊፒንግ ድራገንስ" ለማውጣት በሚጥሩበት ግዜ ተቃዋሚ ሰልፎኞችን ስርሃት ለማስያዝ የሚያገለግል ነው። ይህ መሳሪያ በአሁኑ ወቅት በዩኤስ የሀገር ውስጥ ደህንነት ክፍል/ዲፓርትመንት ኦፍ ሆምላንድ ሰኩሪቲ የሀገር ውስጥ ዝግጁነት የማሰልጠኛ መሳሪያዎች ውስጥ ተካትቷል።

የሚትሮፖልተን ፖሊስ ዲፓርትመንት አባል ስለሆኑ፡ ሲፒኦ ብራድፎርድ አዲስ ፕሬዝደንት በሚማልበት ግዜ፣ የፕሪዝደንት ቀብር በሚኖርበት ግዜ፣ ተቃውሞዎች በሚኖሩበት ግዜ፣ ርችት በሚተኮስበት ግዜ፣ እንዲሁም ሌሎች አስደናቂ የአለም ታሪኮች በሚከናወኑበት ግዜ ሁሉ እንደ ምስክር ሆነው አይተዋል። የሚትሮፖልተን ፖሊስ ዲፓርትመንት አባል መሆን እንዲሁ ስራ ብቻ አይደለም — " በምድር ላይ ከሚደረጉት ትላቅ ትህይንቶች ሁሉ በላይ የሆነውን ትህይንት ለማየት የፊት ለፊት መቀመጫ ላይ እንደመቀመጥ ነው"።

# የስራ ሕይወትዎን የህግ አስከባሪ በመሆን የኤምፒዲ ከዴት ማሰልጠኛ ፕሮግራም በማግኘት ይጀምሩ።



# የፖሊስ ከዴት ማሰልጠኛ ፕሮግራም ውስጥ ይመዝገቡ እና የሀገሪቱ ዋና ከተማ ውስጥ በማገልገል የታሪክ ክፍል ይሁኑ።

## ጠንካራ፣ የተከበረ የስራ ዘርፍ በመምረጥ እውነተኛ የስራ ልምድ ያግኙ። በጭራሽ ሊረሱት የማይችሉትን ተሞክሮ ነው የሚያገኙት !




የፖሊስ ከዴት ስልጠና ፕሮግራም እድሜያቸው ከ17 እስከ 21 ለሆኑና የሜትሮፖልተን ፖሊስ ክፍል ውስጥ በህግ አስከባሪነት ፊልድ ለመስራት ፍላጎት ያላቸው ብቃቱን አሟልተው ለተገኙ ግለሰቦች ስልጠናና የስራ ልምድ ይሰጣል። ፕሮግራሙ የተቀረጸው እጩዎችን ወደ ሜትሮፖልተን ፖሊስ ሹም ቅጥር ፕሮግራም ምግቢያ ለማዘጋጀት ነው።

### ጥቅማጥቅሞች

የምንሰጠው ሁሉን የሚያካትት የጥቅማጥቅም ፓኬጅ የሚያጠቃልለው :

- መነሻ ደሞዝ በአመት 25,315–33,055 ዶላር
- በኮሎምቢያ አውራጃ ዩኒቨርስቲ በኩል ለሚሰጠው የኮሌጅ ትውሽን ሙሉ በሙሉ ይሸፍናል
- የጥርስ እንዲሁም የጤና ጥቅማጥቅሞች
- አመታዊ የስራ እና የህመም ፈቃድ

በተጨማሪም ከዴቶች የዲፓርትመንቱን የቀን ተቀን ተግባሮች እንዲሁም ክፍሉ ካሉት በርከት ያሉ ታሪኮች ጋር መተዋወቅ ሲያስፈልግ ይህንንም ለማድረግ በክፍሉ ውስጥ ባሉ የፖሊስ አውራጃዎችና ለየት ያሉ ዩኒቶች ውስጥ በግዜያዊነት የስራ ምድቦች ላይ በመስራት ነው። ከዴቶች ማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ የፖሊስ እንቅስቃሴዎች ይካፈላሉ፣ እንዲሁም ከዜጎች እና ከጎብኞች ጋር አብረው ይሰራሉ።

### ቢያንስ ቢያንስ ሟሟላት የሚገባቸው ብቃቶች

የፖሊስ ከዴት ስልጠና ፕሮግራም ውስጥ ለመግባት፣ አመልካቾች፦

- የኮሎምቢያ አውራጃ ውስጥ ካሉ ሀይስኩል ውስጥ እየተማሩ ያሉ መሆን ይኖርባቸዋል ወይም ከሀይስኩል የጨረሱ እና በኮሎምቢያ አውራጃ የሚሰጠውን ዲፕሎማ አሊያም ጂሂዲ የተቀበሉ ሊሆን ይገባል።
- እድሜያቸውም ከ17 እስከ 21 ባለው አመት ውስጥ መሆን ይገባዋል፣ እንዲሁም ሲኒየር ሀይስኩል ውስጥ ያሉ ከሆኑ ደግሞበቅጥር ወቅት 21 አመት መሆን የለባቸውም)
- ሁሉን የሚያጠቃልል የህይወት ታሪክ ምርመራ ሁሉ ማለፍ ይኖርባቸዋል፤ ይህም የህክምና ምርመራዎች፣ የድራግ ማጣሪያዎች እንዲሁም የስነልቦና መመዘኛዎችን ያጠቃልላል።
- የአይን ምርመራው ውጤት ቢያንስ 20/100፣ መስተካከል የሚችለው/ኮሬክተብል ወደ 20/30 በሁለቱም አይን በኩል።
- ተቀባይነት ያለው የመንጃ ፍቃድ ያለው አሊያም ሊያገኝ ሂደት ላይ የሆነ
- ወደ ፕሮግራሙ ከመግባትዎ በፊት ተቀባይነት ያለው የሀይስኩል/ኮሌጅ የትምህረት ውጤት ግምገማን የሚያሳይ ትራንስክሪፕት መረጃ ማቅረብ
- በኮሎምቢያ አውራጃ ዩኒቨርስቲ አማካኝነት የሚሰጠውን የኮሌጅ ብቃት ፈተና ማለፍ
- የአካላዊ ጥንካሬ መስፈርቱን የሚያሟላ
- ከፍተኛ የሆነ የስነምግባር ባህርይ ያለው



ተጨማሪ መረጃ ላኩልኝ

### የፖሊስ ከዴት የስልጠና ፕሮግራምን አስመልክቶ ይበልጥ ማወቅ እፈልጋለሁ።

### መዝግቡኝ

እባክዎን ከታች ያለውን ቅጽ ይሙሉ፤ ከዚያም በኋላ ከሜትሮፖልተን ፖሊስ አካዳሚ አንድ ሹም ለፖሊስ ከዴት ስልጠና ፕሮግራም እጩነትዎን አስመልክቶ ያነጋግሮታል።

ስም [Name]

ቁጥር [Number] መንገድ [Street] አፓርትመንት ቁጥር [Apt. #]

የቤት ስልክ [Home Phone] የስራ ስልክ [Work Phone]

የሞባይል ስልክ [Cell Phone] ሌላ ስልክ [Other Phone]

ኢሜል አድራሻ 1 [E-Mail Address 1]

ኢሜል አድራሻ 2 [E-Mail Address 2]

ከዚህ የዲሲ ሀይስኩል ነው የምማረው አሊያም ጨርሼ ተመርቄአለሁ።
[I Attend or Graduated from This DC High School]

የተመረቁበት ቀን (ወይም ለመመረቅ የሚጠብቁት)
[Graduation Date (or Expected)]

የትውልድ ቀን [Date of Birth]